# መቶኛዎችን መተግበር

1. በሰፈራችን ውስጥ በተደረገ ጥናት ሳይክል መንዳት የሚችሉት ልጆች 6% ብቻ ናቸው፡፡ ሳይክል መንዳት የማይችሉት ስንት በመቶ ይሆናሉ?

   ሀ) 78　　ለ) 94　　ሐ) 64　　መ) 88

2. በ6ኛ ክፍል ተማሪዎች  35% የሚሆኑት ተማሪዎች በሂሳብ ትምህርት አማካኝ ውጤት አምጥተዋል ፡፡ የተቀሩት ደግሞ ከአማከኝ በላይ ውጤት አላቸው፡፡ ከአማካኝ በላይ ያመጡት ተማሪዎች ስንት በመቶ ናቸው?

   ሀ) 75　　ለ) 85　　ሐ) 65　　መ) 56

3. በክፍል ውስጥ ካሉት ተማሪዎች ¾ ኛ የሚሆኑት ወንዶች ናቸው፡፡ በክፍላችን ውስጥ ያሉት የሴት ተማሪዎች ስንት በመቶ ይሆናሉ?

   ሀ) 75　　ለ) 22　　ሐ) 85　　መ) 25

4. በአንድ የፊኛ እሽግ ላስቲክ ውስጥ 27% ቀይ ፣ 2/5  ደግሞ ሰማያዊ የቀሩት ደግሞ ነጭ ናቸው፡፡ ነጭ ከለር ያላቸው ፊኛዎች ስንት በመቶ ናቸው ?

   ሀ) 40　　ለ)  35　　ሐ) 33　　መ) 83

LIVEWORKSHEETS

5. በአንድነት ፓርክ ውስጥ አንበሳ፣ ጅብ እና ዜብራዎች አሉ፡፡ 17% አንበሳዎች ሲሆኑ በፓርኩ ውስጥ ካሉት እንሰሳቶች ግማሽ የሚሆኑት ደግሞ ዜብራዎች ናቸው ፡፡ በፓርኩ ውስጥ ከሚገኙት እንሣቶች ጅቦቹ ምን ያህል በመቶ ናቸው ?

ሀ) 92    ለ) 33    ሐ) 67    መ) 45

6. በአየር ንብረት ትንባያ መሰረት ነገ የመዝነብ እድሉ 22% ቢሆን ያለመዝነብ እድሉ ምን ያህል በመቶ ነው ?

ሀ) 88    ለ) 99    ሐ) 78    መ) 68

7. አንድ ባለሙያ በወር ከሚያገኘው 4500 ብር 1/3 ኛ የሚሆነውን በባንክ ተቀማጭ ቢያደርግ፣ ከቀረው ገንዘብ ደግሞ 50% የሚሆነውን ለምግብ ቢያወጣ፣ 20% የሚሆነውን ደግሞ የቤት ኪራይ ቢከፍል ፣ ለምግብ እና ለቤት ኪራይ ያወጣው ከቀረው ብር ላይ ስንት በመቶ ይሆናል ?

ሀ) 80    ለ) 75    ሐ) 70    መ) 60

8. በአንድ የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከር ውስጥ 50 ሊትር ውሃ መያዝ ይችላል ፡፡ ባሁን ሰዓት 30% የሚሆን ውሃ ታንከሩ ውስጥ ተጠራቅሟል፡፡ የውሃ ማጠራቀሚያውን 50% ያህል ለመሙላት ስንት ሊትር ውሃ ያስፈልጋል ?

ሀ) 15    ለ) 9    ሐ) 10    መ) 6

9. እናቴ ከገበያ 10 እንቁላሎችን በ 160 ብር ገዛች ፡፡ ከገዛችው እንቁላል ውስጥ 4 እንቁላሎች ተሰበሩ ፡፡ እናቴ የከሰረችው ገንዘብ ስንት በመቶ ይሆናል ?

ሀ) 45    ለ) 40    ሐ) 35    መ) 25

10. የአንድ ያልታወቀ ቁጥር 30% ውጤት 60 ቢሆን ቁጥሩ ስንት ይሆናል?

ሀ) 40    ለ) 160    ሐ) 250    መ) 200

LIVEWORKSHEETS